# የእግዚአብሔር መንግሥት፡

# ኢትዮጵያ፡

## የቅዱሱ ኪዳን ሕፃናት ልጆቿን፡ ንግግርና ንባብ፥ ጽሕፈትም እያስተማረች የምታሳድግበት

# ሥርዓት።

በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ፡
በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ ተዘጋጅቶ፥
በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ የሚሠራበት።

---

በግእዝ እና በኢትዮጵያኛ፡፡

---

፳፻፪ ዓመተ ምሕረት።



**ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ**
**ኢየሱስ ክርስቶስ**
**ካህኑ ለዓለም፥ ንጉሠ ጽዮን**
***<u>ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u>***

The Conquering Lion of the Tribe of Judah
Jesus Christ
Eternal Priest, King of Zion and
King of Kings of Ethiopia

**ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር**
**ድንግል ማርያም**
**እሙ ወእምነ፥ ንግሥተ ጽዮን**
***<u>ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u>***

Ethiopia stretches out Her Hands to God
The Virgin Mary
Mother of God and Our Holy Mother
Queen of Zion and Ethiopia

# ምስጋናና መታሰቢያ።

ቸሩ እግዚአብሔር፣

በኪዳናውያን ልጆቻችን፣ በሰማዕተና በሰላማዊት አማካይነት፣

ሕፃናት አቤሜሌክንና ቃለሜሌክን ሰጥቶ፣

ቤተሰባችንን፣ እንደገና ስለባረከልን፣

ለልጁ፣ ለኢየሱስ ክርስቶስና ለቅድስት እናቱ፣ ድንግል ማርያም

ለምናቀርበው የማያቋርጥ ምስጋናችን፣

ይህ መጽሓፍ፣ መታሰቢያ ኾኖ ይኖራል።

# መግቢያ

ልዑል እግዚአብሔር፡ በመልኩ ለፈጠረው ሰብኣዊ ፍጡሩ፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ በተፈጥሮው ያስተማረው ፍጹም ትምህርትና በልቦናው ያሳደረው ፍጹም እውቀት አለው፤ ይህንም እውነታ፡ እያንዳንዱ ሰው፡ ወንድ ኾነ ሴት፥ በባሕርዩና በሃይማኖት፥ በልማድና ከታላላቆቹ አዋቂዎች በሚሰማው ይገነዘበዋል። ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ግን፡ ይህ እውነታ፡ ራሱ፡ ህልውናቸው ነው።

"የጥበብ መጀመሪያ፡ እግዚአብሔርን መፍራት ነው!" የተባለው፡ ታዲያ፡ ስለምንድር ነው? የእግዚአብሔር መኖር፥ ደግሞም፡ ይህ መለኮታዊ ትምህርትና እውቀት፡ በእያንዳንዱ ሰብኣዊ ፍጡር ዘንድ፡ ህላዌውና ባሕርዩ በኾነው ኅሊናው ውስጥ፡ አስቀድሞ ስላለ አይደለምን? አዎን! ነው እኮ!

እንዲህ ከኾነ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ታማኝ ባለአደራ የኾነችውና አማናዊ ማንነቷ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ሰውነት የተገለጠው፡ እናት አገራችን ኢትዮጵያ፡ ይህን፡ የቅዱሱን ኪዳን፡ የአደራ ውርስና ቅርስ፡ በወላጆቻችን አማካይነት፥ በቀጥታም፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ዛሬ ላለነው ልጆቿ፡ አስረክባናለች፤ እኛም፡ ጠብቀነውና ሕይወት አድርገነው ያቆየነውን፡ ይህንኑ ውርስና ቅርስ፡ በሃይማኖታዊነቱም ኾነ፡ በምግባራዊነቱ፥ በሕይወታዊነቱም ኾነ፡ በሥርዓታዊነቱ፡ በአባላዊነቱም ኾነ፡ በኹለንተናዊነቱ፡ ለልጆቻችን ማስረከብ ያለብን መኾናችንን አውቀነው፡ ይኸው፡ አኹን፡ በተግባር የምንፈጽመው ተልእኳችን ኾኗል።

ስለዚህ፡ የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ሕፃናት፡ ገና መስማትና ማየት ከሚችሉበት ዐራስነታቸውና አፍ ከመፍታታቸው በፊት ካለው፡ ከልደታቸው የመነሻ ወራት አንሥቶ፡ አስተዳደጋቸው የሠመረ እንዲኾን ለማመቻቸት፥ እንዲሁም፡ ከኢትዮጵያኛው ቋንቋችን፡ የንግግርና የንባብ፥ የጽሕፈትም ሥርዓተ ትምህርት ጋር ለማለማመድ፡ ይህ <u>ቀዳሚ</u> ዝግጅት፡ ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ እንዲያገለግል፡ እነሆ ቀርቧል። እኒሁ ሕፃናት፡ በተለይ፡ ሥርዓተ ትምህርቱን የሚለማመዱት፡ የፊደላችንን ሆህያትና አኀዛት፡ መልካቸውን በማየት፥ ድምፃቸውንም በመስማት ብቻ፡ አስቀድመው ለይተው እንዲያውቋቸው በማድረግ ነው።

እንግዴህ፡ ወላጆችና አሳዳጊዎች፥ ሞግዚቶችና አስተማሪዎች፥ ሌሎችም፡ በሕፃናት አስተዳደግ ተግባርና የማስተማር ሙያ ተሠማርተን የምንገኝ ኹሉ፡ በዚህ ረገድ ያለብንን ግዳጅ ለመወጣት ይቻለን ዘንድ፡ በዚህ ዝግጅት ልንጠቀም ያስፈልገናል። የጠቀሜታውንም ውጤት፡ የኋላ ኋላ፡ በልጆቻችን መልካም ሕይወት ላይ፡ በግዘፍ ተተርጕሞና ለጣፋጭ ፍሬነት በቅቶ እናገኘዋለን፤ ይህም የሚኾነው፡ ይህን፡ ከፈጣሪያችን የተሰጠንን የአደራ ግዳጅ፡ ስንፈጽም ነው፤ እርሱም፡ የመንፈስ ቅዱስ ረድኤት ያልተለየው ይኾን ዘንድ፡ በእኛ በኩል፡ በእውነተኛነትና በታማኝነት፡ በተግባር ላይ የምናውለው ሊኾን ይገባል።

ምናልባት፡ በልዩ ልዩ ምክንያት በማሳበብ፡ ይህን ግዳጃችንን ሳንፈጽም ቀርተን፡ በልጆቻችን ላይ፡ ዛሬ ባለው ትውልድ እየደረሰ ያለውን የመሰለ ጉዳትና መከራ፥ በደልና ሥቃይ ሲደገም ብናይ፡ ለዚህ የኀላፊነት ጉድለት፡ በተጠያቂነት የምንቀርበው፡ በየኀሊናችንና በኅብረተሰባችን፥ በተለይም፡ የዚህ ጥፋታችን ሰለባዎች ኾነው በሚገኙት፡ በእኒሁ ልጆቻችን ፊት ብቻ ሳይኾን፡ እናት አገራችን ኢትዮጵያ በኾነችው፡ በድንግል ማርያምና በልጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ጭምር መኾኑን፡ እዚህ ላይ አበክረን ልናስገነዝብ እንወድዳለን።

ይህ የሕፃናት የአስተዳደግና የትምህርት ሥርዓት፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በዐራስነትና በጨቅላነት ካሉት ሕፃናት ጀምሮ እየተሠራበትና በየጊዜው እየተሻሻለ፡ ዕብሮአቸው እንዲያድግ ተብሎ የተዘጋጀና ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረበ ነው፤ ወደፊት፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ባለሙያዎቻችን እጅ ገብቶ፡ በሥዕል ታጅቦና በተሻለ ዘመናዊ መልክ ተቀነባብሮ፡ የሚያስገኘው ፍሬያማ ውጤት በትክክል እየተገመገመ፥ በተከታታዮቹ የሥርዓቱ መደበኛ ክፍሎቹም እየተሟላና እየተጠናቀቀ እስኪቀርብ ድረስ፡ በተግባር ላይ ውሎ፡ ማገልገሉን ይቀጥላል።

ስለዚህ፡ በዚህ ዝግጅት የምትጠቀሙ ወላጆችና አሳዳጊዎች፥ ሞግዚቶችና አስተማሪዎች ኹሉ፡ የጋራ ግዳጃችን ለኾነው፡ ለዚህ ቍም ነገር፡ ቅን ትችታችሁንና ገንቢ አስተያየታችሁን በመለገሥ፡ በሥርዓቱ ክንውን፥ ጥራትና ምልዓት፡ ያላችሁን ተሳትፎ እውን ታደርጉት ዘንድ እናሳስባችኋለን።

---

# ክፍል ፩ (አንድ)

## ገና አፋቸውን ላልፈቱ፡
## ከዐራስነት እስከ፲-፬ ዓመታት ዕድሜ ላላቸው ሕፃናት።
## እንዲሁም፡
## ለኢትዮጵያኛው ቋንቋ ጀማሪዎች ለኾኑ ትላልቆች።

## የኢትዮጵያ ፊደል፤

### አሌፋቱ (ሆህያቱ) እና አኀዛቱ (ቍጥሮቹ) በዝርዝር፡፡

---

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡
በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# መቅድም።

በዚህ የአስተዳደግ እና የማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ፡ የሚገኙት ተነጋጋሪዎች፡ በአስተማሪና በተማሪ ገጸ ባሕርያት ተመድበው ቀርበዋል:: መግለጫው በሙሉ፡ አስተማሪን፡ በአንስታይ፥ ተማሪን፡ በተባዕታይ አንቀጽ በመግለጽ ተዘጋጅቷል::

እንዲህ የተደረገው፡ ሕያዋን ፍጥረታት የተሠሩት፡ በኹለት፡ የተለያዩ ጾታዎች እንደመኾኑ መጠን፡ እነርሱን በማስተካከል እንዲወክሉ ተብሎ ነው፤ ደግሞም፡ የአስተማሪ ጾታ፡ በአንስታይ የኾነው፡ "እናት"፡ በእናትነቷ ብቻ ሳይኾን፡ ምንም ቢኾን፡ በማናቸውም ኃላፊነቷ፡ በአሳዳጊነቷና በአስተማሪነቷ ጭምር፥ ከሕፃን ልጇ፡ ምንጊዜም የማትርቅ፡ ቀዳሚቷ የቅርብ ባልደረባው መኾኗ ይታወቃል:: የተማሪውም ጾታ፡ በተባዕት የኾነው፡ በወንዱ የአዳም ሰውነት፡ የሴቷን የሔዋንን ምንነትና ማንነት ዐብሮ የመግለጹ ልማድ፡ በእኛ፡ የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ሲሠራበት የተኖረ በመኾኑ ነው።

ከላይ እንደተገለጸው፡ የሕፃኑ አሳዳጊና አስተማሪ፡ እናት ብቻ ሳትኾን፡ አባትም ጭምር፡ አሳዳጊና አስተማሪ ነው፤ ማለትም፡ ኹለቱም፡ ወላጆች፡ በተፈጥሮም ኾነ በሃይማኖት ሥርዓት፡ የሕፃኑና የወጣቱ፥ የጎልማሳውና የትልቁ ሰው ልጃቸው፡ የዕድሜ ልክ አሳዳጊዎችና አስተማሪዎች ናቸው።

ለሕፃኑ፡ አሳዳጊና አስተማሪ የሚኾኑት፡ እኒህ ወላጆችም ኾኑ፡ አሳዳጊዎች፥ ሞግዚቶችም ኾኑ፡ አስተማሪዎች፡ ለዚህ ታላቅ እግዚአብሔራዊ ተልእኮና ኢትዮጵያዊ ግዳጅ፡ ማለትም፡ ለዚህ ሕፃን አሳዳጊነትና አስተማሪነት የበቁ መኾናቸውን፡ ለእየራሳቸውና ለመንፈስ ቅዱስ: በቅድሚያ፡ ማረጋገጥ አለባቸው። ይህም ማለት፡ እያንዳንዳቸው፡ "የፈጣሪያችንና የመምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ የእናት ሃይማኖታችንና አገራችን ድንግል ማርያምም፡ እውነተኞች ባለአደራዎችና ታማኞች አገልጋዮች በመኾን፡ ይህን/ይህችን ሕፃን፡ በመንፈስ ቅዱስ መሪነትና አጋዥነት፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት እውቀት እየኰተኰትሁ ለማሳደግ፡ ፍጹም ፈቃደኛ ነኝ!" ብለው፡ የቃል ኪዳን ምስክርነትን፡ በእየራሳቸው መስጠት ይኖርባቸዋል።

ይህን ቃል ከመግባታቸውና ተልእኳቸውን ከመጀመራቸው በፊት ግን፡ መንፈስ ቅዱስ፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ በየልቦናቸው ካሳደረውና በቅዱሳት መጻሕፍት ከተገለጠው ጋር፡ ለዚህ የአሳዳጊነትና የአስተማሪነት ተግባራቸው የሚረዳቸው፡ አስፈላጊው እውቀት ሊኖራቸው ይገባል፤ ለዚህ ችሎታ ለመብቃትም፡ በዚህ የጎዋ ሰሌዳችን ዋና ገጽ ላይ፥ በልዩ ልዩ መድረኮቹም ውስጥ ተዘርዝረው የቀረቡትን መጻሕፍት፥ መልእክታትና ማብራሪያዎች፡ ቀደም ብለው ያነበቡ ኾነው ይገኙ ዘንድ፡ ራሱ፡ ይኸው ተልእኮ ይጠይቃቸዋል።

እነዚህም፡ ሰባቱን ቅዱሳት ቃል ኪዳናት ስለያዘው፡ ስለቅዱሱ ኪዳን፥ እንዲሁም፡ የእርሱ ስለኾኑት፥ ከእርሱና በእርሱም ስለተገኙት፡ ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፥ ስለኢትዮጵያዊውና ኢትዮጵያዊቷ፥ ከዚህ የተነሣም፡ ኢትዮጵያ፡ ህልውናዋ፡ በአዳምና ሔዋን ልደት የተመሠረተ ኾኖ፡ እስከዛሬ፡ ለ፯ሺ፭፻፱ ዓመታት በነጻነት የቀጠለ፡ የእግዚአብሔር አገርና መንግሥት ስለመኾኗ፥ ልጆቿም፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ ስለመኾናቸው፥ ራሷ፡ የአምላክ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እውነተኛዋና ሕያውቷ ኢትዮጵያ እንደመኾኗ፥ ልጇ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በእርሷ ምክንያት፡ እውነተኛው ኢትዮጵያዊ ስለመኾኑ፥ እነዚህን ስለመሰሉት መለኮታውያን እውነቶች፡ በጥልቀትና በምጥቀት፥ በስፋትና በምልዓት ተብራርተውና ተተንትነው የተገለጹባቸው ናቸው።

## የማሳደግ እና የማስተማር
## ቀዳሚ መመሪያ

በወላጆችና በአሳዳጊዎች፥ በሞግዚቶችና በአስተማሪዎች በኩል ያለው፡ የማሳደጉና የማስተማሩ ተግባር የሚጀመረው፡ ከሕፃኑ ልደትና ከዐራስነቱ ጀምሮ ነው። ስለዚህ፡ ሕፃኑ፡ በጆሮው ስለሚሰማውና በዓይኑ ስለሚያየው ነገር ኹሉ፡ ከባለአደራነታችን የተነሣ፡ የሰውኛው ብቻ ሳይኾን፡ እግዚአብሔራዊው ጥበቃና ጥንቃቄ፥ እንክብካቤም ጭምር፡ እንዳይነፈገው፡ በብርቱ ሊታሰብበት ይገባል።

ይህም ማለት፡ ሕፃኑን፡ "በእግዚአብሔር መልክ ተፈጠረ!" ያሰኘችው፡ ረቂቋ ነፍሱ ብቻ ሳትኾን፡ ይህችው ነፍሱ፡ በዚህ ዓለም ገዝፋ ትኖርበት ዘንድ፡ በፈጣሪ ፍጹም ጥበብ ተሠርቶ የለበሰው፡ ሥጋው ጭምር መኾኑ እንዳይዘነጋ ያስፈልጋል፤ ከእነዚህም ጋር፡ ማለትም፡ ከነፍሱና ከሥጋው ጋር፡ ይኸው ሕፃን፡ በ፵ ቀኑ (ወይም፡ ሴት ከኾነች፡ በ፹ ቀኗ)፡ የእግዚአብሔር ልጅ ኾኖ፡ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ በሚወለደው ኹለተኛ ልደቱ፡ ከፈጣሪው የተጐናጸፈው መንፈሳዊው አካልና ባሕርይ፡ ዐብሮ መኖሩ፡ እሙን ነው።

"እንግዴህ፡ እኒህ ሦስቱ አካላትና ባሕርያት፡ ማለትም፡ ነፍሱም፥ ሥጋውም፥ መንፈሱም፡ ኹሉም፡ የእግዚአብሔር፥ ከእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር ስለኾኑ፡ ለዚህ ሕፃን የሚደረገው የአስተዳደግ ጥበቃና ጥንቃቄ፥ እንክብካቤም፡ ሰውኛው ብቻ ሳይኾን፡ ተፈጥሮአዊው፡ ማለትም፡ እግዚአብሔራዊ የኾነውም እንዳይለየው ያስፈልጋል!" ማለት ነው። ይህም ሲጠቃለል፡ "ለሕፃኑ፡ መልካም አስተዳደግ የሚካኼደው ጥበቃና ጥንቃቄ፥ እንክብካቤም፡ ለአንዱ አካልና ባሕርይ፤ ማለትም፡ ለሥጋ ብቻ ሳይኾን፡ ለነፍሱና ለመንፈሱም ጭምር ሊኾን ይገባል!" ማለት ነው።

ይህ፡ ነፍሳዊና ሥጋዊ፥ መንፈሳዊም ጥበቃና ጥንቃቄ፥ እንክብካቤም፡ ለሕፃኑ በሚደረግበት ጊዜ፡ እኒህ፡ ሦስቱም፡ የሕፃኑ አካላትና ባሕርያት፡ የሥነ ፍጥረት አካላትና ባሕርያት ወደኾኑት ወደውኃና አፈር፥ ወደፀሓይና ነፋስ፡ በተቻለ መጠን፡ ሕፃኑን በማይጎዳ መልክና ይዘት፡ ቀስ በቀስ እንዲቃረቡና እንዲጋለጡ ማድረጉ፡ እጅግ ይጠቅማል።

ጠቃሚነቱም፡ የሕፃኑ ጤንነት፡ አኹን፡ በዚህ ጨቅላነቱ፥ በመካከሉም፡ በልጅነቱ፥ ኋላም፡ በአዋቂነት ዕድሜው፡ በበለጠ የተሟላና የተጠናከረ ኾኖ፡ አያሌ፡ ፀረ-ተፈጥሮና ሰው-ሠራሽ የኾኑትን፡ የዘመኑን በሽታዎች ለመቋቋም የሚችልበትን ኃይልና ብርታት እንዲያገኝ ስለሚረዳው ነው። በሰውኛው፡ ማለትም፡ በዘመናዊው ቍሳቍስና አያያዝ፡ የሕፃኑን የሰውነት አካል፥ ራሱን፥ እጅና እግሮቹን ጭምር፡ ከሚገባው በላይ፡ ያለማቋረጥ፡ በሞቃት አልባሳት መጀቦኑ፡ ለጊዜውና ለዘለቄታው፡ በሕፃኑ ጤንነት ላይ፡ ጠንቀኛ የኾነ ጉዳትን ሊያስከትል እንደሚችል ማወቁ ይበጃል።

የዚህም ምክንያት ግልጽ ነው፦ እነዚህ፡ የሕፃኑ፡ ሦስቱ አካላቱና ባሕርያቱ፡ ማለትም፡ ነፍሱና ሥጋው፡ መንፈሱም፡ ሕፃኑ፡ በዚህ ዓለም በሚያሳልፈው፡ ሥጋዊ ህልውናው፡ ዐብረውት ከሚኖሩትና ከማይለዩት ከአራቱ የሥነ ፍጥረት አካላትና ባሕርያት፡ ማለትም፡ ከአየሩና ከፀሓዩ፥ ከውኃውና ከአፈሩ፡ በመሸፋፈን፡ እንዲርቁ በመደረጉ፡ የሕፃኑ ጤንነት፡ አኹን ኾነ ወደፊት፡ መታወኩ የማይቀር ይኾናል፤ ይህን የመሰለ ሥጋዊ እንክብካቤ የሚደረግለት፡ የሕፃኑ ሰውነት ኹለንተናዊ አካል፡ እንዲህ ስለሚለሳለስና ዓቅመ-ቢስ ስለሚኾን፡ ከዚህ የተነሣ፡ ቀላል የሕመም ተውሣኮችን እንኳ ተከላክሎ ለመቋቋም የሚያቅተው ደካማ ይኾንና፡ ይህ ሕፃን፡ እንደዘመኑ ሰዎች፡ ምንጊዜም፡ ለበሽታ ጎሬነትና ለመድኃኒት ኀተራነት እንዲዳረግ የሚያደርግ ክፉውን ዕጣ መቀበል ግድ ይኾንበታል።

ከዚህ ጠንቀኛ ችግር ለመዳን፡ ሕፃኑን፡ አልፎ አልፎና አንዳንድ ጊዜ፡ በቤትም ኾነ በውጭ፥ በብርድም ኾነ በሙቀት፥ በባዶ እግሩና በቀላል ልብስ እንዲድህ፥ እንዲኼድና እንዲሮጥ፥ እንዲዝናናም መተዉ፥ ገላውንም፡ ቀዝቀዝ ባለ ውኃ ማጠቡ፥ በብርሃን ብቻ ሳይኾን፡ በጨለማም ውስጥ እንዲተኛ ማድረጉ፡ አባል ከኾነበት የሥነ ፍጥረት አካል ጋር ለተስማማ ጤናማ ሕይወት ያዘጋጀዋል።

በሕፃኑ ምግብና መጠጥም በኩል፡ እንዲሁ፡ በተቻለ መጠን፡ የተፈጥሮ የኾነውን ብቻ እንዲመገብ ማድረጉ፡ ለአኹኑም ኾነ ለዘለቄታ ሕይወቱና ጤንነቱ፡ በእጅጉ ይጠቅመዋል። የትኛውም ዓይነት ነገር ቢኾን፥ ወይም፡ ለማናቸውም ግልጋሎት ቢኾን፥ ምንጊዜም፡ ካልታጣና ካልቸገረ በቀር፥ ምርጫም ከኖረ፡ ከሰው-ሠራሹ ይልቅ፡ የእግዚአብሔር የኾነው፡ የተፈጥሮው ስለሚበልጥና ስለሚሻል፡ ወላጆችም ኾን፡ አሳዳጊዎች፥ ወይም ሞግዚቶችና አስተማሪዎች፡ ለሕፃኑ የኹለንተና፡ ማለትም፡ የሥጋና የነፍስ፥ የመንፈስም ደኅንነትና ጤንነት ስንል፡ ምርጫችን፡ የተፈጥሮው ይኾን ዘንድ፡ ልንጠነቀቅበት ይገባል።

እርግጥ፡ የእግዚአብሔር የኾነው፡ የተፈጥሮው ነገር ኹሉ፡ ብቻው "መልካም" ነው፤ ይኹን እንጂ፡ ያም ቢኾን፡ በአግባቡ ካልተጠቀሙበት ሊጎዳ ይችላል። ይህም ሲባል፡ ሰው-ሠራሽ የኾነው ኹሉ፡ ኹሉም "መጥፎና ጎጂ ነው!" ማለት አይደለም።

ፈጣሪ፡ አዋቂና ብልህ፥ ፈልሳፊና ጥበበኛ አድርጎ፡ በመልኩ የፈጠረው ሰው፡ የሠራቸው ሥራዎቹ ኹሉ፡ በመልካምነት ተፈርጀው፡ ሰብአዊዉን ፍጡር፡ የሚያስሞግሱ፥ የሚያገለግሉና የሚጠቅሙ፥ ፈጣሪውን እግዚአብሔርንም የሚያስመሰግኑ ናቸው። ልዩነቱ፡ በፍጡራኑ ርኩሳን መናፍስትም ኾነ፡ በሥጋውያኑ ሰዎች፡ የክፋት አሳብ አመንጪነት ምክንያት፡ እግዚአብሔር፡ ለመልካም የፈጠረው ፍጥረቱም ኾነ፡ ሰዎች ተፈላስፈው የሠሩት የጥበብ ሥራ፡ ለክፋትና ለጥፋት ዓላማ እንዲውል መደረጉ ነው።

ይህን ኹሉ እውነታ፡ ሕፃኑ፡ ከዚህ፡ የጨቅላነት ጊዜው ጀምሮ፡ በእንቡጥ አእምሮው፡ አበክሮ፡ እያወቀውና እየተረዳው፥ እየተገነዘበውም እንዲያድግ ማድረጉ፡ የወላጅነትና የአሳዳጊነት፥ የሞግዚትነትና የአስተማሪነትም ግዳጅ ነው።

ፍጡርና የፍጥረት ወገን የኾነው ነገር ኹሉ፡ የፈጣሪ፡ የእግዚአብሔር ስለኾነ፥ ያም፡ እንደሠሪው እንደእግዚአብሔር፡ ፍጹም መልካም ስለኾነ፥ ያንንም፡ እግዚአብሔር ለመልካም ጥቅምና ለበጎ አገልግሎት ስለፈጠረው፡ እኛ፡ ሰዎች፡ ጥቅምና ጉዳቱን ለይተን አውቀን፡ ያንን ነገር፡ በአግባቡ እስከሠራንበት ድረስ፡ ይበጀናል እንጂ አይጎዳንም፤ በዚህ ምክንያት፡ ፍጡርና የፍጥረት ወገን የኾነው ነገር ኹሉ፡ ሕፃኑን የሚጠቅመው እንጂ የሚጎዳው አይደለም።

ብዙዎቻችን ግን፡ ፍጡርና የፍጥረት ወገን የኾነው ነገር ኹሉ፡ ሕፃኑን የሚጎዳው እየመሰለን፥ ደግ የኾነውንም፡ ወደክፉ በመተርጎም፥ እንዲያውም፡ ከዚህ ይባስ፡ የተፈጥሮ ከኾነው ይልቅ፡ ሰው-ሠራሽ ለኾነው ነገር ኹሉ፡ ቅድሚያንና ብልጫን በመስጠት፡ ሕፃኑን፡ ገና፡ በዚህ ጨቅላ ዕድሜው፡ ወደባሰ ጉዳት የሚወድቅበትን አግጣጫ ልንመራው ስንሞክር እንታያለን። በዚህ አስተሳሰባችንና አድራጎታችንም፡ ሕፃኑን፡ ጎጂ ወደኾነው የአኗኗር ልማድ ውስጥ ገብቶ እንዲጠመድና እንዲታሠር መጋበዛችን ስለኾነ፡ ከዚህ አደገኛ ኹኔታችን ልንታቀብና እንዳናደርገው ልንጠነቀቅ ይገባናል።

ይህን የመሰለው አስተሳሰብና አድራጎት፡ ማለትም፡ ሰው-ሠራሹን በማሞገስ፡ የእግዚአብሔር ሥራ የኾነውን ፍጡርና የፍጥረት ወገን ግን፡ የሚጎዳና የሚከፋ አስመስሎ ማቅረቡ፡ የዚያን ፍጡር፥ ወይም፡ የፍጥረት ወገን፡ ተፈጥሮአዊ ክብር መንካት ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ ፈጣሪውንም መንቀፍ ስለሚኾን፡ ከእኛ ሊወገድ የሚገባው ነው።

የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታችንና የሥነ ፍጥረት እውነታ እንደሚያረጋግጡት፡ ሕፃኑ፡ ከማሕፀን ከወጣበትና ከዚህ የዐራስነት ዕድሜው አንሥቶ፡ ነፍስ እስኪያውቅ ድረስ፡ የሚያየውና የሚሰማው፥ የሚያደርገውም ነገር ኹሉ፣ ኹሉም፡ መልካምና ለመልካም ብቻ ነው። "ክፋት" የሚባለው፡ ጽንሰ ሓሳብ፡ በእርሱ ዘንድ፡ ፈጽሞ የለም።

“ክፉት” ወይም፡ “ሓሰት” የሚባለውን፡ የደግነትና የእውነት ተቃራኒ የኾነውን “መጥፎ” ጽንሰ ሓሳብ፡ ከየራሳቸው ያመነጩት፡ የእግዚአብሔር ተቃዋሚዎች የኾኑ ፍጡራን፡ ማለትም፡ ዲያብሎስና ክፉዎች ሰዎች ናቸው።

ይህ ሕፃን፡ በዚህ ዕድሜው ከሚገኝበት፡ የንጽሓ ባሕርይ ተፈጥሮው የተነሣ፥ ወይም፡ እርሱ፡ ነፍስ ከሚያውቅበት፡ ዓቅመ አዳም (ለሴቷ ዓቅመ ሔዋን) ዕድሜው ደርሶ፥ ምናልባትም፡ ምርጫው ኾኖ፡ ራሱ፡ እስኪቀበለው ድረስ፡ "ክፉት"ን፥ ወይም፡ "ክፉ አሳብ"ን፥ “ሓሰት”ን፥ “ተንኰል”ንና “ቂም በቀል”ን፡ እንኳንስ፡ ከራሱ አሥርጾ ሊፈጽማቸው ይቅርና፡ አእምሮው እንኳ፡ ለይቶ አውቆ ሊቀበላቸው ከቶ አይቻለውም።

ስለዚህ፡ አንዳንድ ጊዜ፡ በእኛ፡ በትልልቆቹ ዘንድ፡ "እንደጥፋት የሚያስቆጥሩ ናቸው!" የምንላቸውና ሕፃኑ የሚያደርጋቸው ነገሮች ቢኖሩ እንኳ፡ በእርሱ፡ በሕፃኑ ዘንድ፡ እንደልማት እንጂ፡ እንደጥፋት ስለማይታዩ፡ ሊያስቆጡን አይገባም፤ ምክንያቱ፡ ይህ መኾኑን ከተረዳን፡ እኛም ከመበሣጨት፥ ሕፃኑንም፡ እንደአጥፊ ቆጥረን፡ ከመቆጣትና ለመቅጣት ከመሞከር መታቀብ ይቻለናል።

ሕፃኑ፡ በፍጹም ነጻነት ኾኖ፡ ኹሉን ማየት፥ ኹሉን መስማት፥ ኹሉን መንካት፥ ኹሉን ማሽተትና ኹሉን መቅመስ ይፈልጋል። እነዚህን ብቻ አይደለም፤ ኹሉን ማወቅና ኹሉን ማድረግም ይፈልጋል። ሕፃኑ፡ ያለዕረፍት፡ በቅብጥብጥነት፡ እንዲህ የሚኾነው ያለምክንያት አይደለም፤ በእግዚአብሔር መልክ ከተፈጠረበት፡ ሰብአዊ ተፈጥሮው የተነሣ መኾኑ፡ በግልጽና በትክክል መታወቅ አለበት።

እንዲህ ከኾነ፡ ያ ነገር የማይጎዳው ከኾነ፡ እንዲያየውና እንዲሰማው ብቻ ሳይኾን፡ ከፈለገ፡ እንዲነካው፥ እንዲያሸትተውና እንዲቀምሰው ማድረጉ አግባብና ጠቃሚ፥ አስፈላጊም ይኾናል። መከልከሉ፡ የተፈጥሮና ሰብአዊ መብቱን መንካትና መግፈፍ ብቻ ሳይኾን፡ ከተከለከለ በኋላ፣ ክፉው ስሜት ያድርበትና፡ የታመቀ ፍላጎቱን ለማርካት፡ እያደባ ቆይቶ፡ ያን ድርጊት፡ የሚጎዳው እንኳ ቢኾን፡ ተደብቆ መፈጸሙ አይቀርም። በዚህ ጊዜ፡ ለወላጅ፥ ለአሳዳጊ፥ ለሞግዚት፣ ወይም፡ ለአስተማሪ የሚተርፈው፡ ብስጭትና ቍጣ፥ ጸጸትና ኀዘን ይኾናል።

እዚህ ላይ፡ ፈጣሪያችንና መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የተናገረውን መሪ ቃል አስታውሰን፡ ልንከተለው ይገባል፤ እርሱም፡ እንዲህ የሚለው ነው፦

**“ይባርካቸው ዘንድ፡ ሕፃናትን አመጡለት፤ ደቀ መዛሙርቱም፡ ያመጧቸውን ገሠፁዋቸው። ጌታችን ኢየሱስ ግን፡ አይቶ ተቈጣ፤ እንዲህም አላቸው፦ ‘ሕፃናትን፡ ወደእኔ ይመጡ ዘንድ፡ ተዉ፥ <u>አትከልክሏቸው</u>! የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እንደእነዚህ ላሉት ናትና። እውነት እላችኋለሁ! የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ እንደሕፃን የማይቀበላት ኹሉ፡ አይገባባትም!’ ሕፃናቱንም አቀፋቸው፤ እጁንም በራሳቸው ላይ ጭኖ ባረካቸው።”** (ማር. ፲፥ ፲፫-፲፮።)

በዚህ መለኮታዊ ቃል መሠረት፡ በዘመኑ፡ በሕፃናት ላይ ያለውን አስተያየትና የአስተዳደግ ልማድ በመከተል፡ ሓዋርያት ሳይቀሩ፡ የፈጸሙትን ስሕተት፡ ጌታ፡ “ሕፃናትን አትከልክሏቸው!” በሚለው ቃሉ፡ እንዴት አድርጎ፡ በቍጣ ሳይቀር፡ እንዳስወገደው እናያለን። ያም ስሕተት፡ የሕፃናቱ ወላጆችና አሳዳጊዎች፥ ሞግዚቶችና አስተማሪዎች፡ “መልካም ነው!” ብለው ያካኼዱትን ተግባር፡ ሓዋርያት አለመቀበላቸውና መቃወማቸው፡ ልማዱ፡ የቱን ያህል፡ ሥር የሰደደ እንደነበረ ያመለክተናል።

ይህን በሚመለከት፡ በሕፃኑ በኩል፡ ለሚገጥመን ችግር፡ መፍትሔው፡ በእኛ፡ በወላጆችና አሳዳጊዎች፥ ሞግዚቶችና አስተማሪዎች ዘንድ፡ “ሕፃኑን ይጎዳሉ!”፥ ወይም፡ “እንደጥፋት ያስቈጥራሉ!” ብለን የምንገምታቸውን ነገሮች፡ ሕፃኑ እንዳይደርስባቸው፥ ወይም፡ አስቀድሞ፡ ከፊቱ እንዲርቁ ማድረግ ይኾናል። ይህን ኹሉ ጥንቃቄ አድርገን፡ ምናልባት፡ አኹንም፡ ሕፃኑ፡ “ጥፋት” የምንለውን ድርጊት ለመፈጸም መሞከሩን የሚቀጥል ኾኖ ብናገኘው፡ ቋንቋውን ባይናገር እንኳ፡ በስሜት ሊገባው ስለሚችል፡ ለዘብ ባለ የርኅራኄ ድምፅና በሕፃናዊ አንደበት፡ “ያን የመሰለውን ጥፋት ማድረግ፡ ራሱንም፥ ሌላውንም የሚጎዳ ስለኾነ፥ አግባብና ትክክልም አይደለምና፡ ‘ኹለተኛ እንዳይደግምህ!’” ብሎ፡ በትዕግሥት ማስረዳትና በጽሙና ማስጠንቀቅ ይበቃል።

ሕፃኑ፡ ምናልባት፡ ይህን የመሰለውን “ጥፋት” ቢደጋግምም፡ በዚሁ መልክ፡ በፍቅርና በርኅራኄ፡ እየገሠፁ መቀጠል እንጂ፡ ወደቍጣና ወደቅጣት መሻገሩ፡ አይጠቅምም፤ ከቁጣውና ከቅጣቱ ይልቅ፡ “ስሕተት” ወይም፡ “ጥፋት” መኾኑን፡ ያለመሰልቸትና በትዕግሥት፡ ደጋግሞ ማስረዳቱ፡ የበለጠና የተሻለ፥ የዘለቄታም መልካም ውጤት አለው። ይህ ኹኔታ የሚቀጥለው፡ ለጥቂት ጊዜ መኾኑንም አለመዘንጋት ነው፤ ሕፃኑ፡ እያደር፣ እያደገና እያወቀ ሲኼድ እኮ፡ ጥፋት ማድረጉን፡ አውቆ ይተወዋል።

እንዲህ ከኾነ፡ በመቆጣትና በመቅጣት ምክንያት፡ በሕፃኑ ላይ ሊደርስ በሚችለው፡ የአካል ብቻ ሳይኾን፡ የአእምሮና የመንፈስ ጠባሳ ጭምር፡ ወላጆችና ሌሎቹ የሕፃኑ ተንከባካቢዎች፡ የሚተርፋቸው፡ ጸጸትና ኀዘን፡ ይኾናል፤ ስለዚህ፡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው እኒሁ ወገኖች፡ በዚህ ነገር አስበውበት፡ ሊጠነቀቁ፥ ከዚህም ጸጸት ይድኑ ዘንድ፡ ይህን የሃይማኖታችንን ሥርዓት አክብረው ሊከተሉት ይገባል።

የሕፃን አስተዳደግ ተልእኮን በሚመለከት፡ ከላይ ከተገለጸው፡ የእውቀት ይዞታ ጋር፡ ወላጆችና አሳዳጊዎች፥ ሞግዚቶችና አስተማሪዎች፡ ሊኖሩዋቸው ከሚያስፈልጉ ጠባያት መካከል፡ <u>ፍቅርና ርኅራኄ፥ ትዕግሥትና ጽናት</u>፡ ቀዳሚዎቹ ኾነው ይገኛሉ።

ስለሕፃኑ ጥበቃና ጥንቃቄ፥ እንክብካቤም፡ “በእኛ በኩል የሚገባንን፡ የባለአደራነትና የኃላፊነት ድርሻችንን እንፈጽም!” ለማለት ያህል እንጂ፡ ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስና ቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም፡ ከቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታችን የተነሣ፡ ለዚህ፡ ለሕፃኑ የቃል ኪዳን ልጃቸው፡ በጸጋ የሚያደርጉለት የአባትነትና የእናትነት ቸርነት አለ።

እርሱም፥ በመንፈስ ቅዱስና በመላእክታቸው አማካይነት፥ የሚደያርጉለት፥ ኹለንተናዊው ጥበቃና ጥንቃቄ፥ እንክብካቤም ነው። ያ መኖሩን፥ በሃይማኖት አውቀንና ተቀብለነው፥ የምንፈጽመው ከኾነ ደግሞ፥ በእኛ ከሚደረግለት፥ ከሰብአዊው ይልቅ፥ ይህ፥ መለኮታዊው፥ የሚበልጥና የሠመረ ፍጹም መኾኑን ስለምንገነዘብ፥ በዚህ ረገድ፥ የወላጅነትና የአሳዳጊነት፥ የሞግዚትነትና የአስተማሪነት ልባችን፥ ሙሉ ዕረፍትን ያገኛል።

አዎን! በዚህ እምነታችን የጸናንና የበቃን ኾነን በምንገኝበት ጊዜ፥ ይህ መታመናችንና ትምክህታችን፥ ከየራሳችን ይልቅ፥ በይበልጥ፥ በዚህ መለኮታዊ ጥበቃና ጥንቃቄ፥ እንክብካቤም ላይ የሚያርፍ ስለሚኾን፥ ከዓቅማችን ማነስና ከኃላፊነታችን ጉድለት የተነሣ፥ ከእኛ ቍጥጥር ውጪ፥ "በሕፃኑ ላይ ምን ጉዳት ይደርስ ይኾን?" የሚለው ሥጋታችንና ጭንቀታችን፥ በእርግጥ ይወገድና፥ ከሕፃኑ ጋር የሚኖረን ሕይወት፥ ከቅዱሳን መላእክት ጋር እንዳለን ዓይነት፥ ሰላምና ደስታ፥ ጸጥታና ዕረፍት የሰፈነበት ኾኖ ይቀጥላል። (ማቴ. ፲፰፥ ፩-፲፬። ማር. ፲፥ ፲፫-፲፮።)

## ሕፃኑ፥ ከሥነ ፍጥረት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት።

መቼም፥ በየቀኑና በየጊዜያቱ፥ ሕፃኑን ዐቅፈን፥ ወይም፥ ዐዝለን፥ ወይም፥ እንኮኮ ብለን፥ በቤትም ውስጥ ኾነ፥ ወይም በውጭ፥ በጋሪ፥ አስቀምጠንም ቢኾን፥ የምናንሸራሽርበት ጊዜ እንደሚኖረን እርግጥ ነው፤ ይኹን እንጂ፥ እኛ፥ የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፥ ይህን፥ የሕፃኑን ሽርሽር የምናካኺደው፥ በሥጋ አቋም ኾነን፥ ለሥጋ ብቻ ብለን ሳይኾን፥ ከላይ በተገለጸው መሠረት፥ በነፍስና በመንፈስም አቋም ኾነን፥ ለነፍስና ለመንፈስም ስንል የምናደርገው እንደኾነ እናውቃለን።

ይህም ማለት፥ ሕፃኑ፥ ከሚተነፍሰው አየርና ከሚሞቀው ፀሓይ፥ ከሚጠጣውና ከሚታጠብበት ውኃ፥ ከሚረግጠውና ከሚቀመጥበት፥ ከሚድህበትና ከሚቆምበት መሬት ጀምሮ፥ በዓይኖቹ እስከሚያያቸው ሣሮችና ተክሎች፥ ቅጠሎችና አበቦች፥ ዛፎችና ፍሬዎች፥ እንዲሁም፥ በምድር ላይ እስከሚንቀሳቀሱ እንስሶችና አውሬዎች፥ ጉንዳኖችና ቢራቢሮዎች፥ ከዛፍ ወደዛፍ፥ በሰማይም ላይ እስከሚበሩ ወፎችና እስከሚናውዘው ደመና፥ እስከሚወርደው ዝናምና እስከሚፈስሰው ወንዝ፥ እስከቆመው ተራራና እስከጥቅጥቁ ደን፥ እነዚህን እስከመሳሰሉት ልዩ ልዩ ፍጡራን ድረስ ያለውን፥ የሥነ ፍጥረት ድንቅ ዓለም፥ ለሕፃኑ እያዘዋወሩ በማሳየት የሚካኼድ ነው። ይህም፥ በሕፃኑ አእምሮ ተቀርጾ፥ ሊጎለምስ የሚገባውን፥ የተፈጥሮና እግዚአብሔራዊ የኾነ እውቀቱን፥ በበለጠ ያዳብርለታል።

በዚህ ጊዜ፡ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን፡ እያንዳንዱን የሥነ ፍጥረት አባልና አጠቃላዩንም ዓለም፡ አልፎ አልፎ እያመለከቱ፡ እንዲህ በሚሉ ቃላት፡ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ፡ በየጊዜውና በየአጋጣሚው፡ በሕፃኑ ጆሮ እንዲፈስስ ማድረጉ፡ አእምሮውን፡ ወደፊት ለሚጠብቀው ሰፊ የእውቀት አዝመራ፡ የለሰለሰ እርሻ አድርጎ ለማዘጋጀት፡ በእጅጉ ያግዛል፡-

"ይህ እኮ፥ አዎን! ይህም ኹሉ እኮ፡ እግዚአብሔር፡ አንተን፡ በመልኩ፡ ማለትም፡ እርሱን ራሱን አስመስሎ፡ ከመፍጠሩና ወደዚህ ዓለም ከመላኩ በፊት፡ በሰላምና በፍቅር፡ ደስ ብሎህና ተመችቶህ፥ ተዝናንተህም፡ እየሠራህ እንድትኖርበት፥ ተዘዋውረህም እየጎበኘህ እንድትቆይበት፡ አስቀድሞ ያዘጋጀልህ የገነት ዓለም ነው። በዘለዓለም ሕይወት ትኖርበት ዘንድ፡ ፈጣሪህ ያሰናዳልህ፡ ሌላ አዲስ ዓለም ደግሞ አለ።

"አኹን በምትገኝበት፡ በዚህ ዓለም፡ እንድትቆይበት፥ ወይም እንድትኖርበት፡ በእርሱ፡ በፈጣሪህ የተወሰነልህ፡ "ዕድሜ" የሚባል ጊዜ አለህ፤ ያም ጊዜ፡ አንተ፡ በፍላጎትህና በምርጫህ፡ ልታረዝመው፥ ልታሳጥረውም የምትችለው ነው።

"ያ ጊዜ ሲያበቃ፡ ማለትም፡ በዚህ፡ የሥጋ አካልህና በዚህ፡ በግዙፉ ዓለም እንድትኖር የተሰጠህን ሕይወትና የምታደርገውን ጉብኝትህን፥ የተላከህበትንም አገልግሎት ስትጨርስ፡ ፈጣሪህ፡ ወደዚያ፡ ወደአዲሱ ዓለም፡ በሹመት ሊወስድህ፡ አንተን የሚጠራበት፡ የደስታ ቀን ይመጣል።

"ለዚያም የምሥራች ጥሪ፡ አንተ፡ ኹልጊዜ፡ ዝግጁ ኾነህ የምትጠብቅ ትኾናለህ። ያ፡ በሹመት የምትኼድበት አዲስ ዓለም፡ ከዚህ፡ አኹን ከምትገኝበት ገነታዊ ዓለም፡ የበለጠ የተሻለና ፍጹም የኾነ ሰላምና ፍቅር፥ ዕረፍትና ብልጽግና፥ ተድላና ደስታ አግኝተህ፡ ከእርሱ፡ ከፈጣሪህና ከእናቱ፡ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጋር፥ ከቅዱሳኑ መላእክትና ጻድቃን ባለሙዋሎቹ ጋር፥ ከእኛም፡ ከኹላችን ጋር ዐብረህ፡ ለዘለዓለም የምትኖርበት ነው።

"አዎን! ይህ ኹሉ የምታየውና ድምፁን የምትሰማው፥ የምትነካውም ፍጥረተ ዓለም፡ ፈጣሪህ እግዚአብሔር እስኪጠራህ፥ በናፍቆትና በፍቅር ዐቅፎም፡ በሹመት፡ ወደእርሱ መልሶ፡ እስኪወስድህ ድረስ፡ የእግዚአብሔር ልጅና መልእክተኛ፥ አገልጋይና እንግዳ በመኾን፡ የምትኖርበትና የምትቆይበት ህልውናና ዓለም ነው!"

ሕፃኑን በማንሸራሸር የሚፈጸመው ይህ ድርጊት፡ በመዓልቱ የብርሃን ጊዜ ብቻ ሳይኾን፡ በምሽቱና በጨለማውም ሰዓት ሊካኼድ ይቻላል፤ ያስፈልጋልም። በዚሁ ጊዜም፡ እንዲሁ፡ በጨለማው ውስጥ ደምቀው የሚታዩትን ጨረቃንና ከዋክብቱን በማመልከት፥ እነዚህ ጭምር፡ የእግዚአብሔር ድንቅ የሥነ ፍጥረት ሥራዎች መኾናቸውን፡ ለሕፃኑ መግለጥ፡ አግባብ ይኾናል።

እርሱ፡ እግዚአብሔር፡ ጨለማውን የፈጠረውና የፀሓዩን ብርሃን ወስዶ፡ አኹን ደግሞ፡ ጨረቃና ከዋክብት፡ በደበዘዘና በሚያብለጨልጭ ብርሃናቸው፡ ሥልጣኑን የሚወስኑበትን፥ ኃይሉንም የሚያዳክሙበትን፡ ጨለማውን ያመጣው፡ ለምን እንደኾነ፡ እንዲህ በሚል ቃል፡ ለሕፃኑ ይብራራለታል፡- "አንተና እኔ፥ ኹላችንም፡ ቀኑን ሙሉ፡ እግዚአብሔር በፈጠረልን፡በፀሓይዋ ብርሃን ስንሠራ፥ ወዲያና ወዲህም ስንል በመቆየታችን፡ ስለሚደክመን፡ እንድናርፍ፥ እንድንተኛና ዕንቅልፍ እንዲወስደን ሊያደርግ፡ አኹን ደግሞ፡ ትናንሽ ብርሃናቸውን የሚሰጡንን፡ ጨረቃዋንና ኮከቦቹን ሰጥቶ፡ ይህን ጨለማ አመጣ፤ ጠዋት፡ ጠንክረንና በአዲስ ጉልበት ኾነን እንድንነሣ ብሎ ነው፡ ይህን ያደረገው።"

ለሕፃኑ፡ እንዲህ ብሎ ማስረዳቱ፡ እርሱ፡ የሚያያቸውና የሚሰማቸው ነገሮች ኹሉ የተፈጠሩት፡ ለእርሱው ጥቅምና አገልግሎት፥ ደስታና ሰላም፥ ዕረፍትና መዝናናት የመኾናቸው እውነታ፡ በአእምሮው ላይ ተቀርጾ፡ እያደገበት እንዲኼድ ያደርጋል።

ይህን የመሰለው፡ አሳሽ ትምህርት፡ ለሕፃኑ የሚሰሰጠው፡ የእግዚአብሔር በኾነው፡ በሥነ ፍጥረቱ አግጣጫ ብቻ ሳይኾን፡ ሰው-ሠራሽ በኾነውም በኩል፡ በዚሁ መልክና ይዘት መካኼድ ይኖርበታል። ምክንያቱም፡ እንደሥነ ፍጥረቱ ኹሉ፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋ እስካለ ድረስ፡ ይህም፡ ሰው-ሠራሹ ነገር ኹሉ፡ የተወለደበትና የሚያድግበት፥ የሚኖርበትም አካባቢ ኾኖ፡ ከእርሱ ጋር ስለሚቀጥል ነው።

ስለዚህ፡ ከተወለደበትና ከሚኖርበት ቤት ጀምሮ፡ ዘወትር የሚያያቸውና የሚሰማቸው፥ የሚነካቸውና የሚይዛቸው፡ ሰው-ሠራሽ ነገሮች ኹሉ የተሠሩት፡ ለእርሱ፡ ሰብአዊ ፍላጎቶች፡ በጎ ጥቅምና አገልግሎት መኾኑን፡ ለሕፃኑ መንገሩ፡ የእውቀት መሠረቱንና ምንጩን፡ አጠናክሮ የተሟላ ያደርግለታል። እነዚህ ሰው-ሠራሽ የተባሉት ነገሮች፡ በቤት ውስጥ እስካሉት ዕቃዎች፥ በውጭም፡ ሲንቀሳቀሱና ሲበሩ እስከሚያያቸው መሣሪያዎች፥ ቆመውና ጸንተው እስከሚመለከታቸው ተቋሞች ድረስ ያሉትን ያጠቃልላል።

ከእነዚህም መካከል፡ የእለቄጥሩን ኃይልና መብራቱን፥ ስልኩንና ነፋስ-ስልኩን፥ ነፋስ-ድምፁንና ነፋስ-ሥዕሉን፥ ሥዕል ማንሻውንና መቅረፀ-ድምፀ ሥዕሉን፥ መቀመሪያውንና ማተሚያዎቹን፥ የኅዋውን አውታርና መገናኛውን፥ የቀረውንም የጽሕፈትና የወጥ ቤት ቍሳቍሱን፥ የሠረገላውን ውኃና የመጸዳጃውን አሠራር ኹሉ፥ ሕንፃውንና መንገዱን፥ የምድር ተሽከርካሪውንና የብረት ሠረገላውን፥ የባሕር ጀልባውንና መርከቡን፥ የአየር ጥያራውንና የጠፈር መንኰራኵሩን፡ ለዓይነት ያህል መጠቃቀስ ይቻላል።

እግዚአብሔር እንደሠራው፡ እንደሥነ ፍጥረቱ ኹሉ፡ እነዚህን የመሰለው፡ ሰው-ሠራሽ የኾነውም ነገር ኹሉ፡ ተሠርቶና ተዘጋጅቶ፥ ተከናውኖና አምሮ የቀረበው፡ ለደግ ስለኾነ፥ ለበጎ ጥቅም፥ አገልግሎትና ዓላማ ካዋሉት ደግሞ፡ ውጤቱ መልካም እንደሚኾን፡ ሕፃኑ፡ ይህን እውነታ፡ ከዚህ ዕድሜው ጀምሮ፡ እንዲያውቀውና እንዲገነዘበው፡ በተቻለ መጠን፡ በየጊዜው፡ አበክሮ መናገሩ፡ በጣሙን ይጠቅመዋል።

*ሰው ግን፡ ያንኑ፡ ለበጎ ዓላማ የሠራውን ነገር፡ ለዚያው፡ ለበጎው ዓላማ እንዲውል በማድረግ ፈንታ፡ ለክፋት ካዋለው፥ ወይም፡ ስላዋለው፡ እስካኹን፡ ራሱን ሊጎዳው፡ እንደቻለ ኹሉ፡ ዛሬና ወደፊትም፡ ሊጎዳው እንደሚችል፡ ከዚሁ እውነታ ጋር አያይዞ፡ ለሕፃኑ መንገሩ ያስፈልጋል።*

*ይህን መንገሩ አስፈላጊ የሚኾንበት ምክንያት፡ ሕፃኑ፡ ነፍስ አውቆ፡ በጎውንም ኾነ ክፋውን ለይቶ፡ ከኹለት፡ አንዱን፡ ማለትም፡ በጎውን፥ ወይም፡ ክፉውን ለመምረጥ ለሚችልበት፡ የዓቅመ አዳም፥ (ወይም፡ የዓቅመ ሔዋን) ዕድሜ ሲደርስ፡ በዚያን ጊዜ፡ ራሱ፡ ተገቢውን ቊርጥ ውሳኔ ለመስጠት፡ ይህ፡ የወላጆች፥ የአሳዳጊዎች፥ የሞግዚቶች፥ ወይም የአስተማሪዎች ተደጋጋሚ የማብራሪያ መልእክት፡ በእውቀቱ ረገድ፡ ብቁና ዝግጁ ስለሚያደርገው ነው።*

---

# ኢትዮጵያዊው ፊደል ፫

# አሌፋቱ

## እና

# አኀዛቱ።

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡
በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# <u>የማስተማሩ ቀዳሚ ተግባር</u>

<u>አስተማሪ</u>፡- *የኢትዮጵያ ፊደል መገለጫ አካልና መሥሪያ አባላት የኾኑትን፡ ከዚህ የሚከተሉትን፡ "አሌፋት"፥ ወይም፡ "ሆህያት"፡ ዐትማ፥ ለየብቻ ለያይታና በየተራ አከታትላ፡ ለሕፃኑ፡ አንድ በአንድ ታሳየው፤* ይህ የሚኾነው፡ የየአንዳንዳቸው መልክ፡ በቅድሚያ፡ በአእምሮው ተቀርጾና ለይቶ ያውቃቸው ዘንድ ነው።

*ከዚያ፡ "ስማቸው፡ ይህ ነው!" ብላ፡ የየአንዳንዳቸውን ምንነት፡ በድምፅ ታሰማው፤* ይህ የሚደረገው፡ የኋላ ኋላ፡ ሕፃኑ፡ አፍ ሲፈታ፡ አስቀድሞ፡ በመልክ ያወቃቸውን አሌፋት፡ በስማቸውም ለይቶ አውቋቸውና አስታውሶ ሊጠራቸው እንዲችል ነው።

እነዚህ ፊደላት፡ እንዲህ ባለ ትላልቅ መጠን ታትመውና ተራብተው፡ ሕፃኑ፡ በየጊዜውና በየአጋጣሚው፥ ሲያልፍ ሲያገድም፣ እንደዘበትም፡ ሊያያቸው በሚችል ቦታዎችና በየግድግዳው ላይ እንዲለጠፉ ኾነው፡ እንዲመለከታቸው ማድረጉ ይረዳል። ደግሞም፡ ባለብስ የመስታወት ወረቀት ማኅደር ባለው፡ ትልቅ ማቀፊያ ደብተርም ውስጥ፡ እያንዳንዱን ቅጠል በማስገባት፡ ያንን፡ በሕፃኑ የምግብ ጠረጴዛውም ላይ ኾነ፡ በመጫወቻ አጥሩ ውስጥ፥ ወይም፡ በመኝታ አልጋው ላይ ተቀምጦም ኾነ፡ ጋደም ብሎ፡ እያገላበጠ እንዲመለከታቸው ማመቻቸቱ፡ እውቀቱን ያጠናክርለታል።

በተጨማሪ፡ ሕፃኑ፡ እነዚህን አሌፋትና አኀዛት፡ (ሆህያትና ቍጥሮች)፡ መልካቸውንና ስማቸውን ለይቶ፡ በአእምሮው ውስጥ ቀርጾ ለመመዝገብና ለማቆየት ይችል ዘንድ፡ አንዳንዴ፡ እንደተውኔት ያለ ቍም ነገርን፡ ከእርሱ ጋር በመዝናናት መጫወትና ማሳየት፡ አንዱ ዘዴ ይኾናል። ይኸውም፡ ሕፃኑን፡ በሩ በተዘጋ፡ በአንድ ክፍል ውስጥ፡ ካዋቂ፣ ወይም፡ መናገር ከሚችል ልጅ ጋር በማስቀመጥ፡ ተውኔቱን፡ ከዚህ እንደሚከተለው ማካኼድ ነው፡-

<u>አስተማሪ</u>፡- *ከውጭ ኾናና አንዱን ሆሄ በእጇ ይዛ፡ በሩን ታንኳኳ!*

<u>በውስጥ፡ ከሕፃኑ ጋር ያለው ሰው</u>፡- "ማነው?" *ይበል!*

<u>አስተማሪ</u>፡- "እኔ ነኝ!" *ትበል!*

<u>ከሕፃኑ ጋር ያለው ሰው</u>፡- "እኔ ማ? ስምሽ ማነው? ተናገሪ?"

<u>አስተማሪ</u>፡- "እኔ፡ አ (ኧ) ነኝ!"

<u>ከውስጥ ያለው ሰው</u>፡- "በእርግጥ፡ አንቺ፡ አ (ኧ) ነሽ?"

<u>አስተማሪ</u>፡- "አዎን! እኔ፡ አ (ኧ) ነኝ!"

<u>ከሕፃኑ ጋር በውስጥ ያለው ሰው</u>፡- "መልካም! አንቺ፡ አ (ኧ)! ግቢ!" ይበል!

*አስተማሪ፡- "እሺ!" በሚል የአዎንታ ቃል፡ የ"አ (ኧ)" ሆሄ የተጻፈበትን ወረቀት፥ ወይም ሰሌዳ፡ እንደጭንብል፡ በግንባሩዋ ላይ አድርጋና በእርሱ፡ ፊቷን ሸፍና፡ በሩን፡ እንደእንግዳ፡ ቀስ ብላ ከፍታ፡ ትግባ!*

*በዚህ ጊዜ፡ በውስጥ፡ ከሕፃኑ ጋር ያለው ሰው፥ ወይም፡ ያሉት ሰዎች፡ "አ!" በሚል ቃለ አንክሮ፡ ብድግ ብለው እያጨበጨቡ፡ "አንቺ ነሽ አ (ኧ)!? እንዴት አደርሽ?" ወይም፡ እንደጊዜው ሰዓት፡ "እንዴት ዋልሽ? ...እንዴ! አንቺ አ (ኧ)! ለመኾኑ፡ እንዴት ቆንጆ ነሽ!? በጣም ታምሪያለሽ!" እያሉ፡ እያቀፉ ሰላምታ ይስጧት!*

*አስተማሪ፡- "አዎን! እኔ፡ አ (ኧ) ነኝ!" የሚለውን ቃል በመደጋገም እየተናገረችና እየቀረበች፡ ከሰዎቹ ሰላምታን ትቀበል! በመጨረሻም፡ ሕፃኑን ዐቅፋ ትሳመው!*

*የቀሩትንም አሌፋት፡ እያንዳንዳቸውን፡ በዚህ መልክና ይዘት በማቅረብ፡ ከሕፃኑ ጋር በቀላሉ፡ ማስተዋወቅ ይቻላል። በተውኔቱም ላይ፡ ከክፍሉ ውጭ ለሚካኼደው የተውኔቱ ክፍል፡ ሌላ ሰውን በመመደብ፡ አስተማሪ፡ ከውስጥ፡ ከሕፃኑ ጋር ተቀምጣ፡ የዚያን የተውኔቱን ክፍል መያዝ ትችላለች።*

ይህን በመሰለ መልክ፡ አሌፋቱን፡ አንድ በአንድ፡ ለሕፃኑ ማስተዋወቁ ይጠቅማል፤ ያስፈልጋልም፤ ለዚህም፡ ታላቅ የኾነ ምክንያት አለ፤ ይኸውም፡ አዳምና ሔዋን፡ ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገሩበት የነበረው፡ ይኸው የግእዝ ቋንቋ፡ ወደፊት፡ በዚህ መጽሓፍ፡ ተስፋፍቶ እንደሚቀርበው፡ ሆህያቱ፡ እያንዳንዳቸው፡ የእግዚአብሔር መታወቂያ ስሞች ስለኾኑ ነው፤ ከዚህ የተነሣ፡ እኒሁ አሌፋት፡ ሕያዋንና መለኮታውያን የመኾናቸው እውነታ፡ ከአኹኑ፡ በሕፃኑ አእምሮ እንዲቀረጽ ማድረጉ አግባብ ይኾናል።

ይህም፡ "አነ ውእቱ፡ አልፋ ወኦ፥ ወአነ ቀዳማዊ፥ ወአነ ደኃራዊ!" ማለትም፡ "አልፋና ኦሜጋ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው፡ እኔ ነኝ!" በሚለው አምላካዊ ቃል ተረጋግጧል። (ራእ. ፳፪፥ ፲፫።)

በዚህ ተውኔት ውስጥ እንደተገለጠው፡ "አ (ኧ)" የሚለው ሆሄ፡ የዋናው፡ የግእዙ እና የኢትዮጵያኛው፡ "አበገደ"ፊደላችን፡ የመጀመሪያው አሌፍ ነው። እርሱም፡ በሥነ ልሳናችን ሥርዓት፡ "ግእዝ" በሚለው፡ በመደበኛው፡ የሆሄ መሠረታዊ ድምፁ፡ "ኧ" ተብሎ ሊነበብ ሲገባ፡ ባዕዳኑ ግብፃውያን፡ በሠነቀሩብን አጕል ልማድ ምክንያት፡ የእርሱ ባልኾነው የተሳሳተ ድምፁ በመጠቀም፡ የዚሁ ሆሄ፡ "ራብዕ" (አራተኛው) በኾነው ድምፁ፡ "ኣ" ብለን እንድናነብበው ተገድደን ኖረናል። ስለዚህ፡ ይህን ስሕተት በመድገም፡ ሕፃኑን፡ ወደዚሁ፡ ስሕተት ብቻ ሳይኾን፡ ከፍተኛ ብሔራዊ ጥፋትና በደል ወደኾነው ጠንቅ መርተን እንዳናስገባው፥ የጥፋቱና የበደሉም ተባባሪ፥ የባዕዳኑም መሣሪያና የስሕተቱ መተላለፊያ ድልድይ እንዳናደርገው፡ በብርቱ ልንጠነቀቅ ይገባናል።

እንደዚሁ ኹሉ፡ “ዐ፥ ሀ፥ ሐ፥ ኀ” ዕጣ ፈንታቸው፡ ልክ፡ እንደ“አ” ኾኖ፡ ኢትዮጵያውያን ሕፃናት፡ እስከቅርቡ ዘመን ድረስ፡ እንዲያነብቧቸው የተማሩት፥ አኹንም፡ ለዚያው፡ ለባዕዳኑ ጥቃት ሰለባነት ተዳርገው፡ እንዲማሩዋቸው እየተደረገ ያለው፡ በዚያው፡ በራብዑ ድምፃቸው፡ “ዓ፥ ሃ፥ ሓ፥ ኃ” ተብለው እንደኾነ ይታወቃል።

በእግዚአብሔር አገርነቷና መንግሥትነቷ፥ ሕዝብነቷም፡ ጸንታ በምትገኘው፡ በቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ዘንድ ግን፡ አኹን፡ ይህ ስሕተት፡ ሰፍኖ እንዳይቀጥል ተደርጓል። ስለዚህ፡ “ዐ” እንደ“ዓ” ሳይኾን፡ በግእዝነቱ፡ “ኧ” ተብሎ መነበብ እንዳለበት ኹሉ፡ እንዲሁ፡ “ሀ፥ ሐ፥ ኀ”፡ እንደ“ሃ፥ ሓ፥ ኃ” ሳይኾን፡ ኹሉም፡ በግእዝነታቸው “ኸ” በሚለው፡ የተለመደው ድምፅ ብቻ ይነበባሉ።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚወሳ፡ ተመሳሳይ ቊም ነገር አለ፤ ይህም፡ “ሠ”ን እና “ፀ”ን፥ እንዲሁም፡ “ኸ”ን እና “ዘ”ን የሚመለከት ነው። ዕብራይስጥንና ዐረብኛን፥ አራማይክንና ግሪክን የመሰሉት፡ የቅርቦቹና የሩቆቹ ሴማውያንና ተዛማች ቋንቋዎች፡ ከአዳማዊው ልሳን፡ ከግእዙ የሠረጹ በመኾናቸው፡ የፊደሎቻቸውና የቃሎቻቸው ብቻ ሳይኾን፡ የሆሄያቱ አጻጻፍና ድምፅ ጭምር መመሳሰል፡ እነዚሁ፡ ቋንቋዎች፡ የአንድ እናት ቋንቋ ልጆች፥ ወይም፡ የአንድ ግንድ ቋንቋ ቅርንጫፎች ለመኾናቸው ማረጋገጫ ነው።

ይኹን እንጂ፡ እነዚሁ፡ በተለይ፡ “ሠ፥ ፀ፥ ኸ” የተባሉት ሆሄያት፡ ከላይ በተጠቀሱት ቋንቋዎች ዘንድ፡ ድምፃቸውን፡ እስከዛሬ፡ እንደነበረ ይዘው ሲቀጥሉ፡ ዐምሓርኛ በተባለው ኢትዮጵያኛ ቋንቋ ዘንድ ግን፡ “ዐ”ን፥ “ሐ”ን እና “ኀ”ን ጨምሮ፡ ይህንኑ፡ የተሠሩበትን፡ የተፈጥሮ ሆሄያዊ ድምፃቸውን ትተው፡ በደረቁ፡ “አ” እና “ሀ” ድምፅ ብቻ የሚነገሩ ኾነዋል።

ይኸውም፡ “ሠ”፡ ድምፁ፡ እንደ“ሰ” ኾኖ፡ ነገር ግን፡ ምላስን፡ በጥርስና ጥርስ መካከል በማድረግ፡ የሚነገር ሆሄ ሊኾን ሲገባ፡ ያ ቀርቶ፡ እንደ“ሰ”፡ በደረቁ ድምፅ ብቻ የሚነገር ኾኗል፤ በዚሁ መልክ፡ “ፀ”፡ ድምፁ፡ እንደ“ጸ” ኾኖ፡ ነገር ግን፡ ምላስን፡ በጥርስና ጥርስ መካከል በማድረግ፡ የሚነገር ሆሄ ሊኾን ሲገባ፡ ያ ቀርቶ፡ እንደ“ጸ”፡ በደረቁ ድምፅ ብቻ የሚነገር ኾኗል። እንዲሁ ደግሞ፡ “ኸ”፡ ድምፁ፡ ከላይ፡ በተገለጠው፡ በትክክለኛው የግእዙ “ሀ” እና በ“ከ” መካከል ያለ ኾኖ፡ ነገር ግን፡ የምላስ ሥር፡ ከትናጋ ጋር ተጣብቆ በሚያልፍ ኃይለኛ እስትንፋስ የሚነገር ሆሄ ሊኾን ሲገባ፡ ያ ቀርቶ፡ እንደግእዙ “ሀ”፡ በደረቁ ድምፅ ብቻ የሚነገር ኾኗል።

ልክ፡ በዚሁ ዓይነት፡ “ዐ”፡ ድምፁ፡ ከላይ፡ በተገለጠው፡ በትክክለኛው የግእዙ “አ (ኧ)” ኾኖ፡ ነገር ግን፡ በጕረሮ ጠብቆ የሚነገር ሆሄ ሊኾን ሲገባ፡ ያ ቀርቶ፡ እንደ“አ”፡ በደረቁ ድምፅ ብቻ የሚነገር ኾኗል፤ እንዲሁ፡ “ሐ”፡ ድምፁ፡ ከላይ፡ በተገለጠው፡ በትክክለኛው የግእዙ “ሀ (ኸ)” ኾኖ፡ ነገር ግን፡ በአፍ ሙሉ የሚነገር ሆሄ ሊኾን ሲገባ፡ ያ ቀርቶ፡ እንደ“ሀ”፡ በደረቁ ድምፅ ብቻ የሚነገር ኾኗል።

ደግሞም፡ “ኀ”፡ ድምፁ፡ ከላይ፡ በተገለጠው፡ በትክክለኛው የግእዙ “ሀ (ኸ)” ኾኖ፡ ነገር ግን፡ በኃይለኛ እስትንፋስ የሚነገር ሆሄ ሊኾን ሲገባ፡ ያ ቀርቶ፡ እንደ“ሀ”፡ በደረቁ ድምፅ ብቻ የሚነገር ኾኗል። ሕዝባዊ የኾነው፡ ዐምሓርኛ፡ “የጨዋ (የማይም) ቋንቋ” የተሰኘው፡ ምናልባት፡ ከዚህ የተነሣ ሊኾን ይችላል!” ብሎ መገመቱ ያስኬድ ይኾናል።

ለብዙ ቋንቋዎች በሚያገለግሉ ሆህያት (የንግግር ድምፖች) የበለጸገው፡ የግእዙና የኢትዮጵያኛው አሌፋታችን፡ በተለይ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ዓለም አቀፍ በኾነው በእንግሊዝኛው ቋንቋ ውስጥ ተዘውትሮ የሚነገረውና የሚስሰማው፡ “the” የሚለው የሆሄ ድምፅ፡ የሌለው በመኾኑ፡ ለ“ሸ” እንደተደረገው ኹሉ፡ ከ“ዘ” ጋር የተዛመደ፡ አዲስ ሆሄን መፍጠር ግድ ኾኗል።

እርሱም፡ በ“ዘ” ሆሄ ዓናት ላይ <u>አንድ የመስመር ምልክትን</u> በመጨመር፡ ድምፁ፡ እንደ“ዘ” ኾኖ፡ ነገር ግን፡ ምላስን፡ በጥርስና ጥርስ መካከል በማድረግ፡ የሚነገር ሆሄ ይኾናል፤ መልኩም፡ ይህን፡- “ዘ፟” እንዲመስል ተደርጓል።

የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው፡ በቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ፡ እነዚህ ሆህያት፡ አኹን፡ አዲስ ኾኖ የታከለውን የ“ዘ፟”ን ሆሄ ጨምረው፡ ጥንቱኑ በተሠሩበት፡ በመደበኛው ድምፃቸው መነገራቸውን ይቀጥላሉ። በእነዚህ ሆህያት ድምፅ ረገድም፡ ለሕፃኑ የሚስሰጠው ትምህርት፡ ይህንኑ መስመር የተከተለ ይኾናል።

እዚህ ላይ፡ ከዚህ ጋር ሊወሳ የሚገባው፡ የእነዚህ ሆህያት ሌላው ልዩ ባሕርያቸው፡ በዚሁ፡ በዐምሓርኛው ቋንቋ፡ የተሳተው፡ የዋናው አገልግሎታቸው ነገር ነው፤ ይኸውም፡ በእነርሱ የሚጻፉ ቃላት፡ ተመሳሳይ መስለው ከሚታዩ ከሌሎቹ ቃላት ተለይተው፡ ራሱን የቻለ ትርጉም ያላቸው መኾኑ ነው።

ለዚህም፡ አጭር ምሳሌን ማቅረብ ይቻላል፡- በግእዙ፡ “ሰአለ” የሚለው ቃል ትርጉም፡ በዐምሓርኛ፡ “ለመነ” ሲኾን፥ “ሠዓለ” ደግሞ፡ “ሥዕል ሣለ” ማለት ነው፤ እንዲሁም፡ “መሀረ”፡ “አስተማረ” ማለት ሲኾን፡ “መሓረ” ደግሞ፡ “ማረ” ማለት ነው። ስለዚህ፡ ሊጠበቅና ሊቀጥል የሚገባው፡ የእነዚህ ሆህያት ጥንታዊዉና መደበኛው ድምፃቸው ብቻ ሳይኾን፡ አገልግሎታቸውም ጭምር መኾኑን፡ ይህ ምሳሌና ከላይ የተሰጠው፡ መጠነኛ ሓተታ ያመለክታል።

በተለይ፡ እነዚህን ሆህያት፥ በአጠቃላይም፡ ኢትዮጵያዊዉን ፊደላችንንና የግእዝ ቋንቋችንን በሚመለከት፡ እዚህ ከተሰጠው መግለጫ በላይ፡ በበለጠ ለመረዳት፡ “ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!” በሚለው፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ በተዘጋጀው መጽሐፍ” ገጽ ፩፻፮-፩፻፲፱ የተሰጠውን ሰፊ ሓተታ መመልከት ነው።

የሆህያቱን የንግግር ድምፅ፡ ከዚህ በላይ በታተተውን መሠረት፡ የሕፃኑ ወላጆችና አሳዳጊዎች፥ ሞግዚቶችና አስተማሪዎች፡ እየራሳቸው፡ በትክክል አውቀውት፡ ለሕፃኑም፡ ሊያሳውቁ ይገባቸዋል። ይህንም በቀላሉ ለማድረግ እንዲያመቻቸው በማሰብ፡ የእነዚሁኑ ሆህያት የንግግር ድምፅ፡ እንደሚከተለው፡ ባጭሩ፡ እንደገና አቅርበነዋል፡-

"አ"፡ በደረቁ ድምፅ የሚነገር ኾኖ፡ "ኧ"፥

"ዐ"፡ በጕረሮ ጠብቆ የሚነገር ድምፅ ኾኖ፡ "ኧ"፥

"ሀ"፡ በደረቁ ድምፅ የሚነገር ኾኖ፡ "ኸ"፥

"ሐ"፡ በአፍ ሙሉ የሚነገር ድምፅ ኾኖ፡ "ኸ"፥

"ኀ"፡ በኃይለኛ እስትንፋስ የሚነገር ድምፅ ኾኖ፡ "ኸ"፥

"ሠ"፡ ድምፁ፡ እንደ"ሰ" ኾኖ፡ ነገር ግን፡ ምላስን፡ በጥርስና ጥርስ መካከል በማድረግ የሚነገር፥

"ፀ"፡ ድምፁ፡ እንደ"ጸ" ኾኖ፡ ነገር ግን፡ ምላስን፡ በጥርስና ጥርስ መካከል በማድረግ የሚነገር፥

"ኸ"፡ ድምፁ፡ በ"ሀ" እና በ"ከ" መካከል ያለ ኾኖ፡ ነገር ግን፡ የምላስ ሥር፡ ከትናጋ ጋር ተጣብቆ፡ ወደውጭ በሚያልፍ ኃይለኛ እስትንፋስ የሚነገር፥

"ቐ"፡ ድምፁ፡ እንደ"ቀ" ኾኖ፡ ነገር ግን፡ የምላስ ማዕከል፡ ከትናጋ ጋር ተጣብቆ፡ ወደውጭ በሚያልፍ ብርቱ የግፊት ኃይል የሚነገር፥

"ዸ"፡ ድምፁ፡ እንደ"ደ" ኾኖ፡ ነገር ግን፡ የምላስ ጫፍ፡ በትናጋ ላይ ዐርፎ፡ ወደውስጥ በሚስሳብ፡ ቀላል እስትንፋስ የሚነገር፥

"ዠ"፡ ድምፁ፡ እንደ"ዘ" ኾኖ፡ ነገር ግን፡ ምላስን፡ በጥርስና ጥርስ መካከል በማድረግ፡ የሚነገር ሆሄ።

ያን፡ ያለፈውን፡ የተሣሣተ ልማድ በማስወገድ፡ ለሕፃኑ፡ የእነዚህን ሆህያት ትክክለኛ መልክ ማሳየት፥ እውነተኛ ስያሜያቸውና የንግግር ድምፃቸውም፡ በዚህ፡ በተስተካከለው ዓይነት መኾኑን ለይቶና አጥርቶ እንዲያውቅ ማድረግ ያስፈልጋል።

እንግዴህ፡ የፊደላቱ ሆህያትና አኀዛት፥ የአሌፋቱ ሰሌዳዎችም፡ እነሆ፡ እንደሚከተለው፡ በየመልኩ ቀርበዋልና፡ እያንዳንዱን ገጽ የያዘውን አጠቃላይ ዝግጅት ዐትሞ በማውጣት፡ ከላይ፡ ቀደም ብሎ በተሰጠው መመሪያ መሠረት፡ በተግባር ላይ የማዋሉ ፋንታ፡ የእኛ፡ የዛሬዎቹ ወላጆችና አሳዳጊዎች፥ ሞግዚቶችና አስተማሪዎች፡ የእያንዳንዳችን ድርሻ ይኾናል።

በዚህ ታላቅ ተልእኮ ረገድ፡ እያንዳንዳችን ያለብንን ግዳጅ እንፈጽምላቸው ዘንድ፡ የሰማዩ አባታችን፡ ልዑል እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስና ዘለዓለማዊት እናት አገራችን ኢትዮጵያ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እነሆ ይጠብቃሉ። ስለዚህ፡ የየበኩላችንን ድርሻ እየፈጸምን፡ ይኸው ተልእኳችን፡ ፍሬያማ ይኾን ዘንድ፡ በድካማችንና በጥረታችን ኹሉ፡ ቸሩ ፈጣሪያችን፡ የማይቋረጠውን የመንፈስ ቅዱስ መርሕና እውቀት፥ ትዕግሥትና ጽናት እንዳያጓድልብን፡ በዘወትሩ ጸሎታችን እንማልደዋለን።

እርሱ፡ አምላካችን እግዚአብሔር፡ ከአባትነት ፍቅሩ የተነሣ፡ ይህ ሕፃንና እርሱን የመሰሉት ኹሉ፡ ኢትዮጵያ ለኾነችው፡ ለቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም፡ ልጆች ይኾኑ ዘንድ፡ በቅዱሱ ኪዳን ፈቅዶ፡ ከጥንት ጀምሮ፡ "የኢትዮጵያ ልጆች!" እያለ የሚጠራቸው፥ እኛም፡ ከእርሱና ከእናቱ፡ በባለአደራነት የተረከብናቸው፡ የዛሬዎቹና የወደፊቶቹ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ሕፃናት ልጆቹ ናቸውና፡ በዚህ መመሪያ ሥርዓታችን መሠረት፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ በጥንቃቄ ጠብቀንና ተንከባክበን፥ በእውቀቱም ኰትኵተን፡ አዎን! ልናሳድግለት ይገባናል።

---

# ከ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# በ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ገ

# ደ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ሀ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ወ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ዘ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ሐ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ጠ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# የ

# ከ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ለ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ፀ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ነ

# ሠ

# ዐ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ሪ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ጸ

# ቀ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ረ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ሉ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ተ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ጸ

# ፐ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ኀ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ፀ



ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ቸ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ኘ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ጀ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ሬቤ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ዘ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ኸ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ቀ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ዷ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።



ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

# ዠ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

አ በ ገ ደ

ሀ ወ ዘ ሐ

ጠ የ ከ ለ

መ ነ ሠ ዐ

ፈ ጸ ቀ ረ

ሰ ተ ፀ ፐ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

ጎ ፀ ሾ ቾ

ኞ ጆ ጬ ዞ

ኾ ቆ ዶ ቮ ዦ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

አ አ አ አ አ አ አ

በ በ በ በ በ በ በ

ገ ገ ገ ገ ገ ገ ገ

ደ ደ ደ ደ ደ ደ ደ

ሀ ሀ ሀ ሀ ሀ ሀ ሀ

ወ ወ ወ ወ ወ ወ ወ

ዘ ዘ ዘ ዘ ዘ ዘ ዘ

ሐ ሐ ሐ ሐ ሐ ሐ ሐ

ጠ ጠ ጠ ጠ ጠ ጠ ጠ

የ የ የ የ የ የ የ

ከ ከ ከ ከ ከ ከ ከ

ለ ለ ለ ለ ለ ለ ለ

መ መ መ መ መ መ መ

ነ ነ ነ ነ ነ ነ ነ

ሠ ሠ ሠ ሠ ሠ ሠ ሠ

ዐ ዐ ዐ ዐ ዐ ዐ ዐ

ፊ ፊ ፊ ፊ ፊ ፊ ፊ

ጸ ጸ ጸ ጸ ጸ ጸ ጸ

ቀ ቀ ቀ ቀ ቀ ቀ ቀ

ረ ረ ረ ረ ረ ረ ረ

ሰ ሰ ሰ ሰ ሰ ሰ ሰ

ተ ተ ተ ተ ተ ተ ተ

ጸ ጸ ጸ ጸ ጸ ጸ ጸ

ፐ ፐ ፐ ፐ ፐ ፐ ፐ

ኀ ኀ ኀ ኀ ኀ ኀ ኀ

ፀ ፀ ፀ ፀ ፀ ፀ ፀ

ሸ ሸ ሸ ሸ ሸ ሸ ሸ

ቸ ቸ ቸ ቸ ቸ ቸ ቸ

ኘ ኘ ኘ ኘ ኘ ኘ ኘ

ጀ ጀ ጀ ጀ ጀ ጀ ጀ

ጬ ጬ ጬ ጬ ጬ ጬ ጬ

ጘ ጘ ጘ ጘ ጘ ጘ

ኸ ኸ ኸ ኸ ኸ ኸ ኸ

ቐ ቐ ቐ ቐ ቐ ቐ ቐ

ዸ ዸ ዸ ዸ ዸ ዸ ዸ

ቨ ቨ ቨ ቨ ቨ ቨ ቨ

ዠ ዠ ዠ ዠ ዠ ዠ ዠ

# አሌፋቱ፡

## <u>በሰባቱ መልካቸውና ድምፃቸው።</u>

# አ ኡ ኢ ኣ ኤ እ ኦ

# በ ቡ ቢ ባ ቤ ብ ቦ

# ገ ጉ ጊ ጋ ጌ ግ ጎ

# ደ ዱ ዲ ዳ ዴ ድ ዶ

ሀ ሁ ሂ ሃ ሄ ህ ሆ

ወ ዉ ዊ ዋ ዌ ው ዎ

ዘ ዙ ዚ ዛ ዜ ዝ ዞ

ሐ ሑ ሒ ሓ ሔ ሕ ሖ

ጠ ጡ ጢ ጣ ጤ ጥ ጦ

የ ዩ ዪ ያ ዬ ይ ዮ

ከ ኩ ኪ ካ ኬ ክ ኮ

ለ ሉ ሊ ላ ሌ ል ሎ

መ ሙ ሚ ማ ሜ ም ሞ

ነ ኑ ኒ ና ኔ ን ኖ

ሠ ሡ ሢ ሣ ሤ ሥ ሦ

ዐ ዑ ዒ ዓ ዔ ዕ ዖ

ፈ ፉ ፊ ፋ ፌ ፍ ፎ

ጸ ጹ ጺ ጻ ጼ ጽ ጾ

ቀ ቁ ቂ ቃ ቄ ቅ ቆ

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መካነ አእምሮ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |

ኀ ኁ ኂ ኃ ኄ ኅ ኆ

ፀ ፁ ፂ ፃ ፄ ፅ ፆ

ሸ ሹ ሺ ሻ ሼ ሽ ሾ

ቸ ቹ ቺ ቻ ቼ ች ቾ

ኘ ኙ ኚ ኛ ኜ ኝ ኞ

ጀ ጁ ጂ ጃ ጄ ጅ ጆ

ጨ ጩ ጪ ጫ ጬ ጭ ጮ

ዠ ዡ ዢ ዣ ዤ ዥ ዦ

ኸ ኹ ኺ ኻ ኼ ኽ ኾ

ቐ ቑ ቒ ቓ ቔ ቕ ቖ

# ደ ዱ ዲ ዳ ዴ ድ ዶ

# ቨ ቩ ቪ ቫ ቬ ቭ ቮ

# ዠ ዡ ዢ ዣ ዤ ዥ ዦ

# አኀዛቱ (ቍጥሮቹ)።

## አኀዝ በግእዝ በኢትዮጵያኛ በእንግሊዝኛ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዐ | ዐልቦ፤ | ባዶ፤ | 0 | Zero |
| ፩ | አሐድ፤ | አንድ፤ | 1 | One |
| ፪ | ክልኤት፤ | ኹለት፤ | 2 | Two |
| ፫ | ሠለስት፤ | ሦስት፤ | 3 | Three |
| ፬ | አርባዕት፤ | አራት፤ | 4 | Four |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፭ | ኅምስት፡ | አምስት፡ | 5 Five |
| ፮ | ሰድስት፡ | ስድስት፡ | 6 Six |
| ፯ | ሰብዐት፡ | ሰባት፡ | 7 Seven |
| ፰ | ሰመንት፡ | ስምንት፡ | 8 Eight |
| ፱ | ተስዐት፡ | ዘጠኝ፡ | 9 Nine |
| ፲ | ዐሠርት፡ | ዐሥር፡ | 10 Ten |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፳ | ዕሥራ፡ | ኻያ፡ | 20 | Twenty |
| ፴ | ሠላሳ፡ | ሠላሳ፡ | 30 | Thirty |
| ፵ | አርብዓ፡ | አርባ፡ | 40 | Forty |
| ፶ | ኀምሳ፡ | ዐምሳ፡ | 50 | Fifty |
| ፷ | ስድሳ፡ | ስድሳ፡ | 60 | Sixty |
| ፸ | ሰብዓ፡ | ሰባ፡ | 70 | Seventy |
| ፹ | ሰማንያ፡ | ሰማኒያ፡ | 80 | Eighty |
| ፺ | ተስዓ፡ | ዘጠና፡ | 90 | Ninety |
| ፻ | ምእት፡ | መቶ፡ | 100 | Hundred |

## ሺ ዐሠርት ምእት፤ ሽሕ፤ 1000=Thousand

## ፼ እልፍ፤ ዐሥር ሽሕ፤ 10,000=Ten Thousand

## ፻፼ አእላፍ፤ መቶ እልፍ፤ 1,000,000=Million

### ሺ፻፼ ትእልፊት፤ ሽሕ አእላፍ፤ 1,000,000,000 = Billion

### ፼፼፼ ምእልፊት፤ እልፍ አእላፉት፤ 1,000,000,000,000 Trillion

---